# የተቋማዊ አደረጃጀት፣የደመወዝ፣ የጥቅማጥቅም እና አመራር ማኅልበቻ የፍላጎት መግለጫ

ይህ የፕሮጀክት ጥናት የድርጅቱን የ5 ዓመት ስትራቴጂዊ ዕቅድ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ የቅድመ-ዝግጅት ማሻሻያዎች ለማድረግ የሚካሄድ ይሆናል፡፡ የድርጀቱን ፣ የቢዝነስ ዘርፎችን እና የድጋፍ ሰጪ የሥራ ክፍሎችን የተዋረድ እና የጎንዮሽ የስራ ግንኙነት በጋራ ዓላማዎች ዙሪያ ማደራጀት ነዉ፡፡ ከአደረጃጀቱ የሚነሱ ለድርጅቱ የሚያስፈልጉ የሰው ኃይል ሁኔታ፣ የሥራ ዝርዝር መግለጫዎች፣የደመወዝና ጥቅማጥቅም እና የሥራ አመራር ማኅልበቻ እና ለስትራቴጂው ተግባራዊነት መደላድል ለመፍጠር የሚረዱ ጥናቶች የሚካሄዱበት ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት ዋና ተግባራት

**የተቋማዊ አደረጃጀት ጥናት፡-** ከድርጅቱ ፍላጎት እና ዓላማ በመነሳት ከድርጅቱ የኃላፊነት ድርሻዎች የሚጠበቁ ተግባራት በጋራ ዓላማዎች ዙሪያ ተሰባስበው እንዲደራጁ በማድረግ የስትራቴጂዉ ግቦችን የማሳካት ባለቤትነትን እና ተጠያቂነትን በየደራጃው ለመፍጠር የሚያስችል ግልጽ የስልጣን ተዋረድን እና የውሳኔ አሰጣጥ ግንኙነት አወቃቀር ይሆናል፡፡

**የሰው ኃይል ሁኔታ ጥናት፡-** ከተቋማዊ አደረጃጀት በመነሳት ሥራው በሚጠይቀው የእውቀት፣ የክህሎት እና የባህሪ ሁኔታዎች ላይ ተመሥርቶ የሚወሰንን የሰው ኃይል ሁኔታ መግለጫዎች ከሥራ መደብ ደረጃ፣ መጠሪያ፣ ብዛት እና የሙያ ዓይነት አኳያ በሠንጠረዥ የሚያጠቃለል እና የአደረጃጀቱ አካል ሆኖ የሚዘጋጅ ጥናት ይሆናል፡፡

**የሥራ ዝርዝር መግለጫ ጥናት፡-** ከተቋማዊ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ሁኔታ መግለጫ በመነሳት በድርጅቱ፣ በሥሩ ባሉ ድርጅቶች እና የድጋፍ ሰጪ የሥራ ክፍሎች ለሚመደቡ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች የየግል የሥራ ድርሻቸውን እና ኃላፊነታቸውን መሠረት ያደረጉ የሥራ መግለጫዎች የሚዘጋጁበት ጥናት ነው፡፡ የሥራ ዝርዝር መግለጫዎች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ለሚመደቡባቸው የሥራ መደቦች እና ደረጃዎች የሚኖራቸውን የኃላፊነትን እና የተጠሪነት ሁኔታ መነሻ በማድረግ ከሥራው የሚጠበቁ ውጤቶችን፣ ለእያንዳንዱ ውጤት የሚቀመጡ ዝርዝር ተግባራትን እና ሥራው የሚጠይቀውን የትምህርት ዝግጅት፣የሥራ ልምድ እና ባህሪ በግልጽ የሚሳይ ጥናት ይሆናል፡፡

**የደመወዝና ጥቅማጥቅም ጥናት፡-** የድርጅቱን፣ የቢዝነስ ዘርፎችንና የድጋፍ ሰጪ ክፍሎችን የአደረጃጀት ተዋረድ፣ የሰው ኃይል ፍላጎት፣ የሥራ መደቦች መጠሪያና ደረጃ መሠረት ባደረገ የሥራዎች ትንትና ውጤት ላይ ተመስርቶ የሚዘጋጅ እና ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ የክፍያ አፈጻጸም ስርአት እንዲኖር ማድረግ ነዉ፡፡ ጥናቱ የድርጅቱን የመክፈል አቅም እና በሀገሪቱ ያለውን የሰው ኃይል ገበያ ሁኔታ መሠረት

በማድረግ የሚካሄድ ይሆናል፡፡ የደመወዝ ስኬል እና የማበረታቻ ሥርዓት ከድርጅቱ ስትራቴጂዊ ዓላማ ስኬት፣ከዓመታዊ የትርፍ ዕድገት እና ከሠራተኞች ሥራ አፈጻጸም ውጤት ጋር በማያያዝ የሚካሄድ ጥናት ይሆናል፡፡

**የአመራር ማጎልበቻ ጥናት፡-** በአሁኑ ጊዜ በድርጅቱ እና በሥሩ ባሉ የቢዝነስ እና ድጋፍ ሰጪ የሥራ ክፍሎች የሚታየውን የአመራር የአቅም እና የመወሰን ክፍተት የሚሞላ እና የስትራቴጂያዊ አመራር ብቃትን ለማሳደግ የሚረዳ ጥናት ነዉ፡፡ ይህ ጥናት በልዩ ሁኔታ የአመራር መረጣ፣ምደባ፣ስልጠና እና የጥቅማጥቅም ዉሳኔዎችን ለማካሄድ የሚረዳ ይሆናል ፡፡ ይህም በድርጅቱ የ5 ዓመት ስትራቴጂዊ ዕቅድ የተቀመጡ ዓላማዎችን እና ግቦችን የማሳካት የሀገር ዉስጥ እና የዉጭ ተሞክሮዎችን መሠረት ያደረገ የአመራር ብቃትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የሥልጠና ፕሮግራሞችን እና ኮርሶችን በማዘጋጀት አቅማቸውን በተከታታይነት የማጎልበት ጥናት ይሆናል ፡፡

# የተቀናጀ መረጃ ስርአት/ኢአርፒ/ የፍላጎት መግለጫ

የድርጅቱ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ከደረጃ1-6 ያሉትን የግንባታ እና ከደረጃ 7-9 ያሉትን የትግበራ ደረጃዎች መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን የትግበራው ሂደት የሚጀምረው ቴክኖሎጂን ተሳቢ በማድረግ ከአውቶሜሽን ነው፡፡ የድርጅቱን የ5 ዓመት ስትራቴጂዊ ዕቅድ ስኬቶችን ከዓመታዊ፣ ከግማሽ ዓመት፣ ከሩብ ዓመታት፣ ከወርሃዊ፣ ከሳምንታት እና ከዕለታት የአፈጻጸም ክትትል፣ ግምገማ፣ ድጋፍ እና ግብረ-መልስ በሚመነጩ መረጃዎች መሠረት ለማረጋገጥ እና በቀጣይነት መሻሻያዎችን ለማካሄድ የቴክኖሎጂ ድጋፍ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ስትራቴጂዉ አዉቶሜት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሲስተሞች በተናጠል ከማልማት ይልቅ አንድ ላይ የሚለሙበት አካሄድ መከተል አዋጪና ጊዜዉ የሚፈልገዉ አማራጭ ነዉ፣ በመሆኑም የተለያዩ ስራ ሂደቶች በአንድ ላይ በመያዝ ተነባቢ ሆነዉ እንዲቀጥሉ የኢአርፒ ሲስተም ማበልጸግ ተገቢ በመሆኑ ከታች የተዘረዘሩ ሞጅሎች ያጠቃለለ ሲስተም መዘርጋትና መተግበር ይጠበቃል፡፡

- ስትራቴጂክ ዕቅድ/ቢኤሲሲ/ የትግበራ ስርአት
- ፋይናንሻል አስተዳደር ስርአት
- የንብረት አስተዳደር ስርአት
- የማህደር አስተዳደር ስርአት
- የወጪናገቢ ንግድ አስተዳደር ስርአት
- የሰዉ ሀብት አስተዳደር ስርአት
- የፊሊት አስተዳደር ስርአት
- የቢዝነስ ኢንተለጀንስ ሲስተም
- የተሸከርካሪ ጥገና አስተዳደር ስርአት